የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

2006 (1998) መግቢያ

በ2006 ዓለምአቀፋዊ የሃይማኖት ነፃነት ዘገባ

የግለሰብ ምርጫ የሆነ እምነት እና መሠረታዊ ነፃነት የአሜሪካዊነት መለያ የመሠረት ድንጋይ እንደመሆኑ፣ የአገራችን መሥራች በሆኑት አባቶቻችን ራዕይም ሥረ መሠረት ያለው ነው። ከአገራችን ልደት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሃይማኖት ነፃነት ከግንባር ቀደም ነፃነቶቻችን አንዱ በመሆኑ፣ አሜሪካኖችም ይህን ነፃነት በአገራችን ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በመላው ዓለም ጭምር ለማስከበር ቆራጥ አቋም ይዘው ኖረዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስ እንደተናገሩት፣ "ለአሜሪካ ከሃይማኖት ነፃነት እና ከሃይማኖታዊ ሕሊና በበለጠ መሠረታዊ የሆነ ጉዳይ የለም። ይህች አገር የተመሠተችው በዚያ መሠረት ላይ ነው፣ እንደዚሁም ይሄ ለዴሞክራሲ ልብ ነው።"

የሃይማኖት ነፃነት በነፃነቶቻችን ዝርዝር አንደኛ ማሻሻያ ላይ የሰፈረ የአሜሪካ "አንደኛ ነፃነት" ነው። እንደዚሁም በአንድነት ተጠቃልለው ለዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እና ለግለሰብ መከበር መሠረት የሆኑትን የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ እና የሕሊና ነፃነትን የሚያካትት እንደመሆኑ፣ የሃይማኖት ነፃነት ለሆኑት ሰብዓዊ መብቶች የማዕዘን ድንጋይ ነው። በዚህ ምክንያት ዛሬ በምሥክርነት የምናስተውለው የዴሞክራሲ ዕድገት ከሃይማኖት ነፃነት እና ከሌሎችም ሰብዓዊ መብቶች ዕድገት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ የተራመደ ነው። የሃይማኖት ነፃነትን ጨምሮ ሰፊ በመሆኑ መስፈርቶች ላይ በመመሥረት እየአንዳንዱን አገር "ነፃ"፣ "በከፊል ነፃ"፣ ወይም "ነፃ ያልሆነ" በማለት በየዓመቱ የሚያከፋፍለው ቤተ ነፃነት የአገር ምደባ ሪፖርቱን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1965 ዓ.ም በለቀቀበት ወቅት 44 አገሮች "ነፃ እንደሆኑ" ገምቷል። እስከ አለፈው ዓመት ድረስ ያ የአገሮች ቁጥር ወደ 89 ከፍ ብሏል። "ነፃ ያልሆኑ" አገሮች ቁጥር በበኩሉ በ1965 ዓ.ም. ከነበረበት 68 ዛሬ ወደ 45 ዝቅ ብሏል።

ዴሞክራሲ እና የመሠረታዊ መብቶች መከበር በመላው ዓለም ወደፊት የተራመዱ ቢሆንም፣ እስከ አሁን ድረስ ብዙ መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ሁለአቀፍ አዋጅን እና ሌሎች ዓለምአቀፋዊ ስምምነቶችንም ለማክበር ያሉባቸውን ሃላፊነቶች በመወጣት ረገድ ከአፍ ያለፈ ተግባር አልፈጸሙም። በጣም ብዙ በሆኑ አገሮች መንግሥታት የሃይማኖት ነፃነትን ለማወቅ እና ለማስከበር እምቢተኞች ናቸው። በአሃዝ የሚቆጠሩ

መንግሥታት ይኸን መሠረታዊ መብት በመፃረር በርትተው ይሠራሉ፡፡ ዛሬ በአንድ አንድ አገሮች አክራሪ ፅንፈኞች፣ አንድን ርዕዮተዓለም ላለመቻቻል እና ለጥላቻ በመጠቀም፣ ሕሊናቸው እንደሚመራቸው መፀለይ ብቻ የሚፈልጉትን ለጥቃቶቻቸው ዒላማ በማድረግ፣ ሃይማኖትን ይበዘብዛሉ፡፡ የሃይማኖት ነፃነትን በትክክል ከሚጠይቁት ጋር አብረን ስንቆምም እንኳን ቢሆን፣ በመንግሥታት ወይም በድርጅቶች ስም ሃይማኖትን አጣምመው በኃይል ለመጠቀም ዓላማዎች የሚያውሉትን፣ ሰብዓዊ ነፃነትን እና ዴሞክራሲን የሚያስናክሉትን ወገኖች በመቃወም አቋማችን ፅኑ ነው፡፡

በዓለምአቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ላይ የሚቀርበው ዘገባ ይኸን ሁለአቀፍ መብት ለማራመድ እና ለማስከበር የሚረዳ መሣሪያ እንዲሆን የተቋቋመ ነው፡፡ ዘገባው በዓለም ውስጥ የሃይማኖት ጭቆና በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ላይ ብርሃን በመፈንጠቅ፣ በዚያም ብርሃን የጭቆናውን ተሳፋፍቶ መራመድ ለማስናከል ይጥራል፡፡ ዘገባው የተመሠረተበት የመመርመር፣ የመመዝገብ፣ እና ጥሰቶችን የመቃወም ሂደት እራሱ ጥሰቶቹን ለማቅለል እና ለመቀነስ ይረዳል፡፡ በጣም ብዙ ሰዎች ድብደባ፣ ማሰቃየት፣ እና መታሰር፣ አንዳንድ ጊዜም እስከ እሚሞቱ ድረስ ግፍ ቢፈጸምባቸውም፣ በእምነታቸው እንደፀኑ የሚቆዩ መሆናቸው ለእምነታቸው ጥንካሬ እና የማይበገር ለመሆኑ ሕያው ምስክር ነው፡፡ በዓለምአቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ላይ የሚቀርበው ዓመታዊ ዘገባ በሃይማኖታዊ መታወቂያቸው፣ በእምነታቸው ወይም በአምልኳቸው ምክንያት በመሰቃት ላይ ስለሚገኙት በብዙ ሚሊዮን ስለሚቆጠሩት በመናገር ለጥንካሬአቸው ይመሰክራል፡፡

ይህ ዘገባ ከአገሪቱ ታሪክ በተፈጥሮ የፈለቀ ነው፡፡ ለእራሳችን እጅግ ተወዳጅ የሆነውን ነገር ሌሎችም እንዲያስከብሩት እና እንዲያቆዩት እናሳስባለን፡፡ እንደ አገር እኛ እራሳችን በዚህ እና በሌሎችም ነፃነቶች ላይ ያለን ድርጊት ፍፁም ስህተት የለሽ አይደለም፡፡ ሆኖም፣ ፈተናውን ተጋፍጦ ይህ ሁለንተናዊ መብት ለሞላው የሰው ልጅ እውን እንዲሆን ከመሥራት ለመሸሽ ወይም ለማፈግፈግ ስህተቶች ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም፡፡

የሃይማኖት ነፃነትን በሞላው ዓለም ለማራመድ ለኘሬዝዳንቱ እና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተጠሪ እና ዋና አማካሪ በመሆን፣ ለዓለምአቀፋዊ የሃይማኖት ነፃነት አምባሳደር በሰፊው እንደመሆኔ፣ የሃይማኖት ነፃነትን ከሚፈልጉ እና ወደፊት ለማራመድ ከሚጥሩ ጋር አብረን መቆም፣ በአንፃሩም ይህን መሠረታዊ መብት የሚያፍኑትን መቃወም የእኔ እና የመሥሪያ ቤቴ ተልዕኮ ነው፡፡ ዓለምአቀፋዊ የሃይማኖት ነፃነት መሥሪያ ቤት በእኔ አመራር በሃይማኖት ነፃነት ላይ አሜሪካ ያላትን ፖሊሲ ለመተግበር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በውጭ አገሮች ባሉ አምባሳደሮቻችን

ከሚገኙ የሥራ ባልደረቦቻችን ጋር ተቀራርበን በመሥራት፣ የዲፕሎማሲ መሣሪያዎች በሙሉ በጉዳዩ ላይ እንዲያተኩሩ ሰፊ እንቅስቃሴ ያደርጋል። ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር በሚደረጉ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ድርድሮች አማካይነት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን እና የአውሮፓ ፀጥታ እና ትብብር ድርጅትን በመሳሰሉ የብዙ ወገን መድረኮች በመሳተፍ፣ ከሰብዓዊ መብቶች እና በእምነት ላይ ከተመሠረቱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች) ጋር በመተባበር፣ እና ከተጠቁት ጋር በመገናኘት፣ ጭቆናው በሚገኝበት በማናቸውም ሥፍራ መቃወሚያ የሚሆኑ ስትራቲጂዎችን ቀይሰን በተግባር ላይ እናውላለን። በዓለምአቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ላይ ይኸን ስምንተኛውን ዓመታዊ ዘገባ ለኮንግሬስ እና ለሕዝብ ስናቀርብ፣ ኘሬዚደንት ቡሽ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ራይስ በዚህ ጉዳይ ላይ ለሰጡት ጠንካራ እና ጠንቃቃ አመራር፣ እንደዚሁም ሁለቱም የኮንግሬስ ፓርቲዎች ለሰጡት ድጋፍ ምሥጋናዬን መግለጽ እወዳለሁ። በተጨማሪም ለተጨቋኞቹ በመቆም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ለሚሠሩት በርካታ ግለሰቦች ሁላችንም የምናቀርበው ምሥጋና አለብን።

ቤተ ነፃነት አገሮችን የመደበበት ዝርዝር እንደሚያሳየው ሁሉ፣ መልካሙ ዜና በአንድነት ወደፊት እየገፋን መሆናችን ነው። ያም ሆኖ ገና ከባድ ፈተናዎች እንዳሉብን በግልጽ ይታያል። ኘሬዚደንት ቡሽ እንዳሉት "አሜሪካ የነፃነትን አለኝታነት ወደፊት እያራመደች በምትገኝበት ጊዜ ነፃነት አሜሪካ ለዓለም የሰጠችው ገፀ በረከት ሳይሆን፣ በዚህች ዓለም ውስጥ ለሚገኝ ለእያአንዳንዱ ወንድ እና ሴት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መሆኑን እናስታውሳለን። ይህ ሐቅ ሰዎች በያሉበት ሁሉ የሃይማኖት ነፃነት እንዲኖራቸው፣ እና ሁሉም የተሻለ፣ ብሩህ እና በይበልጥ ሰላማዊ የሆነ የወደፊት ሕይወት እንዲኖረው ለመርዳት የምናደርገውን ጥረት ያራምደዋል።" በእምነታቸው የተነሳ በዓለም ዙሪያ በመሰቃየት ላይ የሚገኙ ወኔያማ ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት በዚህ ዓመታዊ ሪፖርት ይታሰቡበት። እንደዚሁም፣ በመጠኑም ቢሆን ለምኞታቸው ማበረታቻ እና ታሪካቸው ሳይነገር ላለመቅረቱ፣ ወይም ስቆቃቸው በዓለም ጉዳዮች ኘሬስ ያልተረሳ ለመሆኑ ጥቂት ተስፋ ይሰጣቸው።

ጆን ቪ. ሃንፎርድ 3ኛ፣ ዓለምአቀፋዊ የሃይማኖት ነፃነት አምባሳደር በሰፊው

መስከረም 5 ቀን 1999 ዓ.ም ተለቀቀ

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ኢትዮጵያ

ዓለምአቀፋዊ የሃይማኖት ነፃነት ዘገባ 1998 (2006)
በዲሞክራሲ፣ ሰብዓዊ መብቶች፣ እና የሠራተኛ ቢሮ የተሰቀቀ

ሕገ መንግሥቱ የሃይማኖት ነፃነት እንዲኖር ይደነግጋል፣ መንግሥትም በጠቅላላው ድንጋጌውን በአሠራር አክብሯል። ሆኖም፣ የአካባቢ ባለሥልጣኖች አንዳንድ ጊዜ ይህን መብት ተፃርረውታል።

ለአብያተ ክርስትያናት፣ ለመስጊዶች፣ እና ለመካነ መቃብሮች መሬት ሲያስፈልጋቸው የአካባቢ ሹማምንት አድልዎ እንደሚያደርጉባቸው አንዳንድ የኘሮቲስታንት እና የሙስሊምቡድኖች ቅሬታ ማስማታቸውን ቢቀጥሉም፣ በዚህ ዘገባ በተሸፈነው ጊዜ ውስጥ የሃይማኖት ነፃነትን በማክበር ረገድ ምንም ያህል ለውጥ አልነበረም። በጠቅላላው በማኅበረሰቡ ውስጥ ባሉት የሃይማኖት ቡድኖች መካከል ያለው ወዳጃዊ ግንኙነት ለሃይማኖት ነፃነት አስተዋፅኦ ማድረጉን ቀጥሏል። በአጠቃላይ ሲታይ፣ በሃይማኖቶች መካከል ግጭት እና ቁርቁዞዎች ትንሽ ጨምረዋል። መንግሥት አንዳንድ የሙስሊም ወገኖችን መንቀፉን ቀጥሏል። በባህላዊ ሙስሊሞች እና ከሳዑዲ ዐረቢያ ድጋፍ እንደሚያገኝ በተዘገበለት በዋሃቢ አንጃ መካከል እስላምን በመተርጐም ላይ መካረር እንደነበረ ተዘግቧል።

የአሜሪካ መንግሥት ሰብዓዊ መብቶችን ወደፊት ለማራመድ ላለው ጠቅላላ ፖሊሲ አካል በማድረግ፣ የሃይማኖት ነፃነትን ጉዳዮች ከመንግሥት ጋር ይወያይባቸዋል።

ክፍል 1. የሃይማኖት ስታቲስቲክ

አገሪቱ 472,000 ካሬ ማይል የቆዳ ስፋት አላት፣ የሕዝቡም ቁጥር 74 ሚሊዮን ያህል ነበር። ከሕዝቡ ውስጥ ከ40 እስከ 45 በመቶ የሚገመተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ-ክርስትያን (ኢኦቤክ) ምእመን ነበር። ኢኦቤክ በትግራይ እና በአማራ የሰሜን ክልሎች የበላይነትን ይዞ ነበር።

ከሕዝቡ 45 በመቶ ያህል የሚሆነው ሱኒ ሙስሊም ነበር። እስላም በመሥራቅ ሱማሌ እና በአፋር ክልሎች፣ እንደዚሁም በምሥራቅ እና በደቡብ የኦሮሚያ ዋነኛ ክፍሎች የበላይ ነበር።

ክርስትያን ወንጌላውያን እና ጴንጤቆስጤያዊ ቡድኖች በፍጥነት እያደጉ ያሉ እምነቶች መሆናቸውን በመቀጠል፣ ከሕዝቡ ውስጥ 10 ከመቶ ያህል የሚሆነውን ይዘዋል። እንደመካነ ኢየሱስ እና ቃለ ሕይወት ያሉት የቆዩ/የፀኑ አብያተ ክርስትያናት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት (ደብብሕክመ)፣ በምዕራብ እና ማዕከላዊ ኦሮሚያ፣ እንደዚሁም በከተማ አካባቢዎች ጠንካራ ነበሩ። በምዕራብ በጋምቤላ ውስጥ የመካነ ኢየሱስ ተከታዮች ከሕዝቡ 60 ከመቶ የሚሆነውን ወክለዋል። የወንጌላዊ ቤተ ክርስትያን ተከታዮች (ኢቫንጀሊካል ቸርች ፌሎውሺፕ) በሃይማኖታዊ ዣንጥላው ሥር 23 የተለያዩ እምነቶች እንዳሉ ተናግረዋል።

ምሥራቃዊ አምልኮ እና የላቲን አምልኮ ሮማዊ ካቶሊኮች ቁጥር ከ500,000 በላይ ነበር። ከ7,500 በላይ የጀሆቫ ምሥክሮች እና 105 የንጉሥ ግዛት አዳራሾች በአገሪቱ ውስጥ እንደነበሩ ተዘግቧል። አይሁዶች፣ አረመኔያውያን እና ሌሎች ባህላዊ አገር በቀል አምልኮዎች ከሕዝቡ ቀሪውን ክፍል በአብዛኛው አቅፈዋል። በአዲስ አበባ እና በሰሜን ጐንደር፣ በአማራ ክልል አንዳንዶቹ ቀደምቶቻቸው ከብዙ ምዕተ ዓመታት በፊት ከአይሁዳዊነት ወደ ኢትዮጵያዊ ኦርቶዶክሳዊነት መለወጥ (መጠመቅ) እንደተገደዱ (ፊሊስ ሞራ) ተናግረዋል። ኤቴይስቶች ወይም በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ በጣም ጥቂት ነበሩ። ትክክለኛ ቁጥር ማግኘት ባይቻልም፣ በአገሪቱ ውስጥ በሃይማኖት ሥነ ሥርዓቶች በጠቅላላው ንቁ ተሳትፎ ነበር።

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የውጭ አገር ሚስዮናውያን ቡድኖች በአገሪቱ ውስጥ ሠርተዋል። የሚስዮን ሥራን ስፖንሰር ያደረጉ ወይም የደገፉ የኘሮቴስታንት ድርጅቶች የሚከተሉትን ያከተቱ ነበር፡- ባፕቲስት ባይብል ፌሎውሺፕ፣ ኒው ነቨናንት ባፕቲስት ቸርች፣ የባፕቲስት ወንጌላዊ ማኅበር፣ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን (ከሉተራን ቤተክርስትያን ጋር የተዛመደ)፣ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስትያን (ከሰርቨስ ኢን ሚሽን ጋር የተዛመደ)፣ የሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስትያን (ከሰዊዲሽ ፊላዴልፊያ ቤተ ክርስትያን ጋር የተዛመደ)፣ ገነት ቤተ ክርስትያን (ከፊኒሽ ሚሽን ጋር የተዛመደ)፣ የኢትዮጵያ ሉተራን ኘሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስትያን፣ እምነተ ክርስቶስ፣ ሙሉወንጌል ቤተ ክርስትያን፣ መሠረተ ክርስቶስ (ከሜኖናይት ሚሽን ጋር የተዛመደ)፣ ጴንጠቆስጤያውያን የጀሆቫ ምሥክሮች፣ እና የኋላ ጊዜ መላእክት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስትያን (ሞርሞንስ) ጭምር ንቁ ሚሲዮናዊ ሥራ ነበራቸው።

ክፍል 2. የሃይማኖት ነፃነት

የሕግ/የፖሊሲ ማዕቀፍ

ሕገ መንግሥቱ የሃይማኖት ነፃነት እንዲኖር ይደነግጋል፣ መንግሥትም በጠቅላላው ድንጋጌውን በአሠራር አክብሯል። ሆኖም፣ የአካባቢ ባለሥልጣኖች አንዳንድ ጊዜ ይህን መብት ተፃርረውታል። ሕገ መንግሥቱ መንግሥት እና ሃይማኖት እንዲለያዩ ይጠይቃል፣ አንድ የመንግሥት ሃይማኖት እንዳይኖርም ይከለክላል። መንግሥትም እነዚህን ድንጋጌዎች በአሠራር በጠቅላላው አክብሯል። በ1996 ዓ.ም በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ውስጥ የሥልጣን ሽኩቻ በተፈጠረበት ጊዜ የፌዴራሉ መንግሥት የምክር ቤቱን ሹማምንት አሿሿም እንደሚፈልገው በማመቻቸት፣ በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቷል።

መንግሥት የሃይማኖት ቡድኖች እንዲመዘገቡ ይጠይቃል። የሃይማኖት ተቋማት እና አብያተ ክርስትያናት፣ መንግሥታዊ እንዳልሆነ ድርጅቶች (መያዶች) ሁሉ፣ በፍትሕ ሚኒስቴር ያላቸውን ምዝገባ በእየሦስት ዓመት ማደስ አለባቸው። ይህ የምዝገባ ጥያቄ "አዲሶቹን ሃይማኖቶች"፣ በተለይም የኘሮቴስታንት አብያተ ክርስትያናትን፣ አያያዝ በሚመለከት መንግሥት ወደፊት አለመራመዱን ወይም አለመሻሻሉን ያንፀባርቃል በማለት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጉባዓ ገልጿል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን በማናቸውም ጊዜ በመንግሥት ዘንድ ተመዝግባ አታውቅም፣ በዚህ የተነሳም በማናቸውም ጊዜ አጸፋዎች አልገጠሟትም። የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ከዘጠኝ ዓመት በፊት ከተመዘገበ በኋላ፣ ዳግመኛ ተመዝግቦ አያውቅም። በእነዚህ ማበላለጦች ላይ ሌሎች የሃይማኖት ቡድኖች ተቃውሞ ቢያሰሙም፣ ከመንግሥት እኩል አያያዝ አላስገኘም። በሕግ ፊት እኩል አያያዝ እንዲኖር በአገሪቱ የሮማው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ልዑክ (አምባሳደር) ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ጽፈዋል። መካነ ኢየሱስ፣ ወንጌላዊ ፌሎውሺፕ፣ የሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስትያን፣ አብያተ ክርስትያናት "ከመያዶች የተለየ ሥፍራ" ሊኖራቸው እንደሚገባ አምነዋል። ሆኖም፣ በዚህ ዘገባ በተሸፈነው ጊዜ ውስጥ የመንግሥት ፖሊሲ ለውጥ አልነበረም።

በሕጉ መሠረት፣ የልማት ተግባሮች የሚያካሄድ ማናቸውም የሃይማኖት ድርጅት የልማት ክንፉን ለይቶ በፍትሕ ሚኒስቴር ዘንድ እንደ አንድ መያድ ማስመዝገብ

አለበት፡፡ ለመመዝገብ እያንዳንዱ የሃይማኖት ድርጅት አንድ የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት እና ከውስጠ ደንቡ አንድ ቅጅ፣ የድርጅቱ መሪ የሕይወት ታሪክ፣ እና የመታወቂያ ደብተሩ ፎቶኮፒ ጋር ማቅረብ አለበት፡፡ አንድ ቡድን ሳይመዘገብ መቅረቱ ሕጋዊ አቋም እንዲነፈግ በማድረግ፣ የባንክ ሂሳብ ከመክፈት ወይም በማናቸውም የፍርድ ሂደት ከመሳተፍ አሳግዶታል፡፡

የሃይማኖት ቡድኖች የቀረጥ ነፃ እውቅና አልተሰጣቸውም፡፡ ለአብያተ ክርስትያናት፣ ለትምህርት ቤቶች፣ ለሐኪም ቤቶች መሥሪያ እና ለመካነ መቃብሮች የሚሆን የመንግሥት መሬት በነፃ እንዲገለገሉበት ይሰጣቸዋል፡፡ ሆኖም፣ የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች እና ሆስፒታሎች፣ የሠሩበት ጊዜ ርዝመት ዋጋ ሳይኖረው፣ በማናቸውም ጊዜ በመንግሥት ለመዘጋት እና መሬቱም ለመወረስ የተጋለጡ ናቸው፡፡ የሃይማኖት ቡድኖች፣ እንደማናቸውም ግለሰብ ወይም የንግድ ሥራ ድርጅቶች ሁሉ፣ መሬት/ቦታ እንዲሰጣቸው ለክልል እና ለአካባቢ መስተዳድሮች ማመልከት አለባቸው፡፡ የሃይማኖት ድርጅቶች የቀረጥ ነፃ እውቅና እንዲሰጣቸው በማድረግ ሕጉ እንዲሻሻል ለመግፋት ከየሃይማኖቱ በጥምር የሚደረገው ጥረት ቀጥሏል፡፡

በቁጢጥ ባዮች የተገነቡ መስጊዶች በ1996 ዓ.ም. እንዲፈርሱ ተደርጓል የሚሉ አቤቱታዎች ከቀረቡ በኋላ፣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በሕገ ወጥነት በቁጢጥ ባዮች የተሠሩ ሌሎች መስጊዶችን ለማፍረስ የነበረውን ዕቅድ አቁሞታል፡፡

በሃይማኖቶች መካከል በተፈጠሩ አብዛኞቹ ጭቅጭቆች መንግሥት ከማናቸውም ጋር ከመወገን ተቆጥቦ ገለልተኛ ሽምጋይ ለመሆን ሞክሯል፡፡ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች የሃይማኖት ቡድኖችን ጉዳይ የሚመለከት አንድ የፌዴራል ተቋም እንዲመሠረት ጠይቀው ነበር፡፡ ሆኖም፣ ይህ ዘገባ እስከ ሽፈነው ጊዜ መጨረሻ ድረስ ምንም የተወሰደ እርምጃ አልነበረም፡፡

ሃይማኖትን እና መንግሥትን የሚለያየውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ መንግሥት በትምህርት ቤቶች፣ የሕዝብም ሆኑ የግል፣ የሃይማኖት ትምህርት አይፈቀድም በማለት ተርጉሞታል፡፡ የካቶሊክ፣ የኦርቶዶክስ፣ የወንጌላውያን፣ እና የሙስሊም ትምህርት ቤቶች ሃይማኖትን እንደ አንድ የትምህርት ኮርስ ማስተማር አልተፈቀደላቸውም፡፡ በአዲስ አበባ የሚገኘው የመንግሥት የትምህርት ቢሮ አብዛኞቹ የግል ትምህርት ቤቶች የሥርዐተ ትምህርታቸው አካል አድርገው የሚሰጡዋቸው የግብረ-ገብት (ሞራልስ) ትምህርቶች ከሃይማኖት ተፅእኖ ነፃ አይደሉም በማለት ቅሬታውን ገልጿል፡፡ አብያተ ክርስትያናት የሰንበት ትምህርት እንዲኖራቸው ተፈቅዶላቸው ነበር፡

በመስጊዶችም ቁርአንን ያስተምሩ ነበር፣ የሕዝብ ትምህር ቤቶች የሃይማኖት አዝማሚያ ያላቸውን ጨምሮ ክበቦችን ማቋቋም ተፈቅዶላቸው ነበር፡፡

መንግሥት የክርስትያን እና የሙስሊም በዓላትን በይፋ ያውቃል፡፡ እንደዚሁም ሙስሊሞች ወደ መስጊድ ሄደው ለመፀለይ ጊዜ እንዲኖራቸው ዓርብ ዕለት ለምሳ ሁለት ሰዓት መፍቀዱን እንደቀጠለ ነው፡፡ በመንግሥት የታወቁ የክርስትያን በዓላት ልደት፣ ጥምቀት፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ እና መስቀል፣ እንደዚሁም የእስላም በዓላት ኢድ አል-አድሃ (አረፋ)፣ የነቢዩ መሐመድ ልደት፣ እና ኢድ አል-ፈጥርን (ራማዳን) ያካትታሉ፡፡ በተጨማሪም የአዲስ አበባ የንግድ ኮሌጅ ሙስሊም ተማሪዎች የቀትር በኋላ ፀሎታቸውን በአቅራቢያው በሚገኝ መስጊድ ማድረስ እንዲችሉ፣ የቀትር በኋላ ክፍሎች የትምህርት ሰዓት በ7:30 እንዲጀመር ያቀረቡትን ጥያቄ መንግሥት ፈቅዷል፡፡

የሃይማኖት መሪዎችን በዋነኛ የማኅበረሰብ ዘመቻዎች በማካተት፣ በሃማኖቶች መካከል መግባባት እንዲኖር መንግሥት እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ በኤችአይቪ/ኤይድስ ላይ ብሔራዊ የአጋርነት መድረክ በተቋቋመበት እና በ1997 ዓ.ም. አንቲሬትሮቫይራል ሕክምና በተጀመረበት ጊዜ የሁሉም ዋነኛ ሃይማኖቶች መሪዎች ተገኝተው ነበር፡፡ በዚህ ዘገባ በተሸፈነው ጊዜ ውስጥ በሃይማኖቶች መካከል ምንም የሃሳብ መለዋወጥ አልተደረገም፡፡

በሃይማኖት ነፃነት ላይ የተደረጉ እቀባዎች

በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳይኖሩ መንግሥት ያግዳል፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የሃይማኖት የፖለቲካ ፓርቲዎች አልነበሩም፣ እገዳውም በአሥራር አልተፈተነም፡፡

ከመንግሥት ፈቃድ ተሰጥቶት የሚሠራ የሃይማኖት ድርጅት የልማት ክንፍ ካልሆነ በስተቀር፣ መንግሥት ለውጭ አገር የሃይማኖት ሠራተኞች የሥራ ቪዛ አልሰጠም፡ ሆኖም፣ ይህ ፖሊሲ በሙስሊሞች እና በኦርቶዶክስ ክርስትያኖች ላይ በተመሳሳይነት እንዲፀና አልተደረገም፡፡ በዚህ ዘገባ በተሸፈነው ጊዜ ውስጥ ለሃይማኖት ድርጅቶች የልማት ሥራዎች መንግሥት ፈቃዶችን ሰጥቷል፣ ግን ለሃይማኖት ሥራዎቻቸው አይደለም፡፡ የአገር ውስጥም ሆነ ወይም የውጭ አገር፣ ለሁሉም የሃይማኖት ቡድኖች ፈቃዶች ያስፈልጋሉ፡፡ ተለይቶ ባልተነገረ ምክንያት የፍትህ ሚኒስቴር ቢያንስ ለአንድ ባሕላዊ የኦሮሞ የሃይማኖት ድርጅት፣ ዋቃፌታ፣ ፈቃድ ነፍጓል፡፡

የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት የውጭ አገር ኢማሞችን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይከታተላል፣ እንደዚሁም የዋሃቢ ተፅእኖ መስሎ የሚታየውን ያጣራል፡፡

በኘሬስ ሕግ መሠረት አንድን ሃይማኖት በሌላው ላይ ማነሳሳት ወንጀል ነው፡፡ የሃይማኖት መሪዎችን በሚመለከት የስም/የዝና ማጉደፍ ተፈጽሞብናል የሚሉ ካሉ፣ እንደ ወንጀል ጉዳዮች ክስ እንዲመሠረት የኘሬስ ሕጉ ይፈቅዳል፡፡ መንግሥት ዝና ማጉደፍ ተፈጽሞብኛል በማለት በ1994 ዓ.ም. በሁለት ጋዜጠኞች ላይ የመሠረተውን ክስ በሚመለከት ምንም አዲስ ነገር አልነበረም፣ ይኖራል ተብሎም አይገመትም፡፡ ሪፖርቱ በሸፈነው ጊዜ ውስጥ የሃይማኖት ቡድኖችን በማነሳሳት ወይም የሃይማኖት መሪዎችን ዝና በማጉደፍ ክስ የተመሠተባቸው ጋዜጠኞች አለመኖራቸውን ኢሰመጉ ዘግቧል፡፡

በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ላይ ያሉት ደንቦች በጣም ጥብቅ መሆናቸውን እና በመጽሐፍ ቅዱስ እና በሌሎችም የሃይማኖት መጣጥፎች ላይ የሚጠየቀው የጉምሩክ ቀረጥ ከመጠን በላይ ነው በማለት ወንጌላውያን የሃይማኖት መሪዎች ቅሬታ አሰምተዋል፡፡ ሆኖም፣ በስጦታም ይሁን ወይም በሌላ መንገድ በመጡ መጻሕፍተ ቅዱሳን እና የሃይማኖት መጣጥፎች ላይ መከፈል ያለበት የጉምሩክ ቀረጥ በሌሎች ወደ አገር በሚገቡ መጻሕፍት ላይ ከሚከፈለው ጋር እኩል ነው፡፡ በመንግሥት እና በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ቤተክርስትያን በመካነ ኢየሱስ መካከል የቀጠለው ውይይት በዚህ ጉዳይ ላይ መሻሻል አሳይቷል፡፡ በ1998 ዓ.ም. ፓርላማ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ መጻሕፍትና የታተሙ መጣጥፎች ላይ የነበረውን ቀረጥ በማንሳት ለጉዳዩ ተፈላጊውን ውጤት አስገኝቷል፡፡

ካለፉት ዓመታት በተለዩ ሁኔታ፣ ሙስሊም ሴቶች ራሳቸውን የሚሸፍኑበትን ሻሽ በሚመለከት የተዘገቡ ችግሮች አልነበሩም፡፡ ሆኖም፣ አንድ ሙስሊም የአስታማሚነት ተማሪ ሕመምተኞችን በምትጐበኝበት ጊዜ እግሮቿን ጭምር የሚሸፍነውን ቀሚስ (ሂጃብ) አልለውጥም በማለቷ የተፈጠረውን ሁኔታ የሃይማኖት መሪዎች በቀሚስ ፈንታ እራሷን በሻሽ እንድትሸፍን በማድረግ የተሳካ ሽምግልና ፈጽመዋል፡፡

የአናሳ ሃይማኖት ቡድኖች ለሃይማኖት አገልግሎት የሚውል የመንግሥት መሬት/ቦታ በመመደብ ረገድ አድልዎ የሚፈጸሙባቸው ስለመሆኑ ቅሬታ ገልጸዋል፡፡ ለአብያተ ክርስትያናት እና ለመካነ መቃብሮች መሬት ሲያስፈልጋቸው የአካባቢ ሹማምንት አድልዎ እንደሚፈጽሙባቸው የኘሮቴስታንት ቡድኖች ቅሬታ ገልጸዋል፡፡ እንደ መጠ

ስለሚቆጠሩ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን እና ከኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ጋር ሲመዛዘን፣ በቦታ/መሬት ምደባ አንፃር ተገቦ ስለመሆናቸው ወንጌላውያን መሪዎች ቅሬታ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ከመንግሥት መሬት/ቦታ በማግኘት በኩል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን በበለጠ ችግር እንዳለበት ቅሬታውን ገልጿል፡፡ ሌሎች ግን ለመስጊድ የሚሆን ቦታ በማግኘት ረገድ የተመረጠ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ሕገ መንግሥቱ የሃይማኖት ትምህርት እና አስተዳደር ተቋማትን የመመሥረት ነፃነት መኖሩን ቢደነግግም፣ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን የተቀደሰ ከተማ በሆነው በአክሱም አንድ መስጊድ መገንቢያ ቦታ እንዲሰጣቸው ሙስሊም መሪዎች በተደጋጋሚ ያቀረቡዋቸውን ጥያቄዎች የአካባቢው ባለሥልጣኖች ባለመቀበል ቀጥለዋል፡፡ የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ሹማምንት የአክሱም ከተማን በሚመለከት ይኸን ድንጋጌ በሰፊው መተርጐም አልፈለጉም፣ የፌዴራል መንግሥትም ይህን አቋማቸውን አልለወጠውም፡፡ በ1988 ዓ.ም. አገሪቱ ሪፐብሊክ ከሆነች ቦኋላ ሙስሊሞች መሬት ማግኘት ችለዋል፡፡ በ1996 ዓ.ም. አንድ የሙስሊም ቡድን በአክሱም መስጊድ ለመሥራት የሞከረ ቢሆንም፣ የክልሉ መንግሥት ፈቃድ ሳይሰጥ የተገነባ ስለነበረ ለአመፅ የተነሳሳ የአካባቢው ሕዝብ አፍርሶታል፡፡ የአካባቢው ሹማምንት ግንባታ እንዳይቀጥል የሙስሊም ማኅበረሰቡን አዝዟል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለአብያተ ክርስትያናት በቂ ሥፍራ መስጠት በኘሮቴስታንት ቡድኖች ዘንድ አንድ ዋና ጉዳይ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ እነዚህ ቡድኖች ከመስከረም 1996 ዓ.ም. እስከ ሐምሌ 1997 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ውስጥ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ቢያንስ ሃያ አብያተ ክርስትያናት መሥራቷን፣ ሌሎች ቡድኖች ግን ትልቅና የሚስቡ አዲስ ሕንፃዎች መሥራት እንዳልተፈቀደላቸው አውስተዋል፡፡

ጥምቀትና መስቀልን የመሳሰሉ የኦርቶዶክስ ክርስትያን በዓላት በአዲስ አበባ ከተማ ትልቅ በሆኑት ሁለት የሕዝብ አደባባዮች፣ በጃንሜዳ እና በመስቀል አደባባይ እንደሚከበሩ በአንፃሩ የኢድ አል-ፈጥር አከባበር ግን ታዋቂነቱ ዝቅተኛ በሆነው የአዲስ አበባ ስቴዲየም እንዲከበር መደረጉን በማውሳት፣ የአገሪቱ የሃይማኖት በዓላት በትክክለኛነት የማይከበሩ መሆናቸው እንደሚያሳስባቸው የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት አሰምቷል፡፡ ለዚህ በዓል አከባበር የሚሰማማ ግንባታ ለማድረግ ቦታ እንዲሰጠው የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ያቀረበው ጥያቄ በዚህ ዘገባ የተሸፈነው ጊዜ እስከተጠናቀቀ ድረስ በእንጥልጥል ነበር፡፡

አመች ሥፍራ ከመንግሥት ስላልተሰጣቸው የጀሆቫ ምስክሮች አባላት በከተማው ውስጥ እና በአገሪቱ በሙሉ ለእራሳቸው ቦታዎች መከራየትን ቀጥለዋል፡፡ ሆኖም፣ በኦሮሚያ ከክፍያ ነፃ የሆኑ አንዳንድ ቦታዎች የፀሎት ቤት እንዲሠራባቸው ለአንዳንድ የሃይማኖት ቡድኖች ተሰጥተዋል፡፡

በደርግ አገዛዝ ወቅት በመንግሥት የተወረሱ ንብረቶቻቸውን ለማስመለስ መካነ ክርስቶስ/ሜኖናይት ቤተ ክርስትያን፣ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስትያን፣ ሰባተኛ ቀን የአድቬንቲስት ቤተ ክርስትያን፣ እና የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ያደረጉት ጥረት ውጤት ለማስገኘት ምንም ያህል አልገፉም፡፡

የመካነ ክርስቶስ/ሜኖናይት ቤተ ክርስትያን ደርግ ከሥልጣን ከተወገደ በኋላ ፀሎት ቤቱን ማስመለስ ቢችልም፣ በ1996 ዓ.ም. መንግሥት እንደገና ይዞበታል፡፡ መንግሥት የወሰደውን እርምጃ ባለው ሕጋዊ የአሠራር ዘዴ ተከላክሏል፡፡

ሦስት የተማሪዎች ሆስቴሎችን እና ሁለት ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ፣ ከመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስትያን በደርግ አገዛዝ የተወረሱ ንብረቶችን መንግሥት አልመለስም፡፡ እነዚህ ጉዳዮች አሁንም መፍትሄ ያላገኙ መሆናቸውን የመካነ ኢየሱስ አመራር ገልጿል፡፡

የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶችም በደርግ አገዛዝ የተወሰዱባቸውን ንብረቶች፣ ሁለት ሆስፒታሎች ጭምር፣ ለማስመለስ ያደረጉት ጥረት ወደፊት አልተራመደላቸውም፡፡ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤትም ከርዕሰ ከተማው ውጭ በተመሳሳይ ሁኔታ የተወረሱበትን ንብረቶች ለማስመለስ ሙከራውን ቀጥሏል፡፡ በፌዴራል ድንጋጌ መሠረት በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ቤቶች ተመልሰውለታል፡፡ ሆኖም፣ በክልል ሕግ ሥር የሚገኙት ትላልቅ እና ዓይን የሚስቡ ሕንፃዎች ገና የሚመለሱ ናቸው፡፡ መንግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያንን የሚያቀርብ ለመሆኑ አንድ የሚጠቀስ እና አንዳንድ አስተሳሰብ ቢኖርም፣ የመንግሥት ሹማምንት ግን ምንም ማበላለጥ እንደማይደረግ ገልጸዋል፡፡

በሃይማኖት ነፃነት ላይ የተፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑ አድራጎቶች

የሙሉ ወንጌል መሪ የነበሩትን ቄስ (ፓስተር) ደመጠውን ገድለዋል ተብለው በ1994 ዓ.ም. የተከሰሱት ሁለት ወንዶች ክስ መደመጥ እንደቀጠለ ሲሆን፣ ሰዎቹም በእስር ቤት ናቸው፡፡ ቄሱ የተገደሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን ቄሶች

የተመራ ለአመፅ የተነሳሳ ቡድን በኃይል ወደ ቤታቸው በገባበት ጊዜ እንደነበረ ተነግሯል፡፡ ይህ ዘገባ የሚሸፍነው ጊዜ ሲያከትም የክሱ ጉዳይ በእንጥልጥል ነበር፡፡

ሌላው ተመሳሳይ ነገር የአንድ ሙስሊም ወንድ በአንድ ኘሮቴስታንት መገደል፣ በሃይማኖት የተነሳ ሆኖ ባይታይም፣ ባለሥልጣናት ኘሮቴስታንቱን በግድያ ወንጀል የከሰሱት ሲሆን፣ ጥቂት ድረ-ገጾች "ሰማዕትንት" ብለው ዘግበውታል፡፡

በመጋቢት 1998 ዓ.ም. ክርስትያን ተብሎ የሚታመን እና አዕምሮው የተቃወሰ ግለሰብ ቀሚሴ በተባለ የአማራ ክልል ከተማ ነብዩ ሙሐመድን የሚያንኳስሱ አስቂኝ ስዕሎች ሳለ፡፡ የአካባቢው ሙስሊሞች፣ የእስልምና አክራሪ የተባሉ፣ ተቃውሞ አደራጅተው በቀሚሴ ከተማ ያካሄዱት አመፅ በበርካታ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት፣ አራት ወንጌላውያን አብያተ ክርስትያናት ላይ ውድመት፣ በ1.4 ሚሊዮን ብር በተገመተ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ አመፁን ያካሄዱት ታግተው ይህ ዘገባ በተጠናቀቀበት ገዜ ምርመራው እየተካሄደ ነበር፡፡

ሚያዝያ 7 ቀን 1998 ዓ.ም. ማንነታቸው ያልታወቀ፣ ነገር ግን ከአካባቢው ማኅበረሰብ ውስጥ ሙስሊሞች ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦች ስብስብ፣ በጂጂጋ በሚገኘው የኢትዮጵያ ተዋህዶ አማኑኤል ቤተ ክርስትያን ላይ የእጅ ቦምብ በመወርወር በበርካታ ተሳላሚዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ ይህ ዘገባ በተጠናቀቀበት ጊዜ ፖሊሶች ወንጀለኞቹን በመፈለግ ላይ ነበሩ፡፡

በደቡብ ዩኒቨርሲቲ አንድ ክርስትያን ተማሪ ሚያዝያ 12 ቀን 1998 ዓ.ም. ቁርዓንን ማርከሱ በሞላ አገሪቱ ሙስሊሞችን አስቆጥቷል፡፡ ፖሊስ ሁኔታውን መርምሮ ወንጀለኛውን አግቷል፡፡ ይህ ዘገባ በተጠናቀቀበት ወቅት ጉዳዩ በእንጥልጥል ነበር፡፡

በአገሪቱ ውስጥ የሃይማኖት እስረኞች ወይም ታጋቾች ስለመኖራቸው ዘገባዎች አልነበሩም፡፡

ክፍል 3. የማኅበረሰብ ተገቢ ያልሆኑ አድራጎቶች እና ማበላለጥ

በጠቅላላው በኅብረተሰቡ ውስጥ በሃይማኖት ቡድኖች መካከል የነበረው ወዳጃዊ ግንኙነት ለሃይማኖት ነፃነት አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ሆኖም፣ በሃይማኖት ቡድኖች መካከል አንዳንድ አነስተኛ ግጭቶች ቀጥለዋል፡፡ እነዚህም የተከሰቱት በአብዛኛው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች እና በወንጌላዊ ኘሮቴስታንቶች፣ በወንጌላዊ ኘሮቴስታንቶች እና በሙስሊሞች፣ እንደዚሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች

እና በሙስሊሞች መካከል ነበር፡፡ በተጨማሪም በሃይማኖቶች መካከል መካረር የነበረባቸው እና በሃይማኖት ቡድኖች መካከል መተቻቸት የነበረባቸው አንዳንድ ጠባብ ሥፍራዎች እንደነበሩ ቀጥለዋል፡፡

እንደ ጴንጤቆስጤያውያን ያሉ አዳዲስ እምነቶች አባላት ከሕዝብ ለገጠማቸው ግልጽ ተቃውሞ የፖሊስ ጥበቃ ጠይቀዋል፡፡ በሃይማኖት ሹማምንት እና በሃይማኖት አባላት ላይ በዝቅተኛ ደረጃ ያነጣጠሩ አካላዊ እና በንግግር ማስጨነቅ እንደነበሩ እና የጥቃት ሰለባዎቹም ከአካባቢ ባለሥልጣኖች ጥበቃ ስለመጠየቃቸው በርካታ ዘገባዎች ነበሩ፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መሪዎች አንዳንድ ጊዜ ፕሮቴስታንቶች የኦርቶዶክስ የተቀደሱ ቀናትን እና ልምዶችን እንደማያከብሩ ዘግበዋል፡፡ ሙስሊሞችም አንዳንድ ጴንጤቆስጣዊ ሰባኪዎች ሰብኩት/ፀሎት በሚያካሄዱበት ወቅት እስላምን እንደሚያንቋሽሹ ዘግበዋል፡፡ አንዳንድ የሙስሊም እና የፕሮቴስታንት መሪዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስትያን የበላይነቷን ለማሳዬት ያላት ፍላጐት በሃይማኖት ማኅበረሰብ ወስጥ ቁጣ እና አትንኩኝ ባይነት ስለመፍጠሩ ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

በአብዛኞቹ ክልሎች ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች እና ሙስሊሞች በጠቅላላው አንዱ የሌላውን የሃይማኖት ሥነ ሥርዓት ከማክበርም ባሻገር፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በሃይማኖቶቹ መካከል ጋብቻን እና የሃይማኖት መለወጥን በሚመለከት መቻቻል ነበር፡፡ በአዲስ አበባ የተለያዩ እምነቶች ያሉዋቸው ሰዎች አብረው ጐን ለጐን ይኖራሉ፡፡ አብዛኞቹ የከተማ አካባቢዎች የሁሉንም የሃይማኖት እምነቶች ቅይጥ ያንፀባርቃሉ፡፡ የሮም ካቶሊክዊት ቤተ ክርስትያን እና የወንጌላዊ ፕሮቴስታንት የሃይማኖት ክፍሎች የጤና እንክብካቤን እና ትምህርትን የመሳሰሉ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን የየሃይማኖታቸው አባል ላልሆኑ እና ለአባሎቻቸውም ይሰጣሉ፡፡

የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት በሙስሊም ማኅበረሰቡ ውስጥ የውጭ ዋሃቢ ተፅእኖ እየጨመረ በመምጣቱ ላይ ያለውን ስጋት መግለፁን ቀጥሏል፡፡ በሳውዲ ገንዘብ በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አማካይነት ወደ አገሪቱ የሚገባው ገንዘብ ኢትዮጵያዊ እስልምና ያልሆኑ የውጭ ተፅእኖዎችን ስለሚያራባ አሳሳቢነቱ ከፍ እያለ መምጣቱን የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ገልጿል፡፡

በ1997 ዓ.ም. የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት በውስጡ የነበሩትን አክራሪ ዋሃቢስቶች ታግሎ ሥራ አስፈፃሚ አባላቱን በመሉ በጠንካራ ፀረ-ዋሃቢስቶች ተክቷል፡፡ መንግሥት በጉዳዩ ላይ ጥቅም እንዳለው ለማሳየት፣ አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ በምርጫው ስብሰባ ላይ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የዋሃቢስቶች

በምክር ቤቱ መቀመጫ ማግኘት የሚያሳስበው መሆኑን የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ገልጿል፡፡

በግንቦት 1997 ዓ.ም. ብሔራዊ ምርጫውን እንዲታዘቡ የሃይማኖት ተቋሞች 1,554 አባሎቻቸውን በሞላ አገሪቱ አስማርተው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት 558 ታዛቢዎችን፣ የኘሮቴስታንት የተለያዩ የሃይማኖት ክፍሎች 607፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን 359፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን 30 ታዛቢዎችን አሠማርተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ሰልፎች ከተደረጉ በኋላ የሃይማኖት ድርጅቶች መሪዎች፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን፣ የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት፣ የመካነ ኢየሱስ ወንጌላዊት ቤተ ክርስትያን፣ እና የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ጭምር ሰኔ 2 ቀን 1997 ዓ.ም. ሰላም እንዲሰፍን ጥሪ አድርገዋል፡፡

የእልስምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት መሪዎች ከአካባቢው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን መሪዎች ጋር በመተባበር፣ በኦሮሚያ ክልል በኮፈሌ ወረዳ ማኅበረሰብ አባላት ላይ በፖሊቲካዊ ተነሳሽነት በሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም. የተፈጸመው ግድያ ያስከተለውን ውጥረት ማርገብ ችለዋል፡፡ ሃይማኖታዊ ቀስቃሽነት የነበረውን አንድ ጥንድ ግድያ ተከትሎ እና በአካባቢው ብዙሃን የሆኑት ሙስሊሞች በክርስትያኖች ላይ ማስጨነቅ/ማዋከብ ማካሄዳቸው ከተዘገበ በኋላ የሃይማኖት መሪዎች ተቀራርበው በመሥራት እየጨመረ የነበረውን ሁከት እና ብጥብጥ ማስቆም ችለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስትያን ቄሶች በአፈንጋጭ ሙስሊም ግለሰቦች ዒላማ ውስጥ ስለገቡ፣ የአካባቢው ኢማሞች መጠለያ እንደሰጧቸው እና ጥበቃ እንዳደረጉላቸው መዘገቡን ከሰሙ በኋላ፣ የሁለቱም እምነቶች መሪዎች ሰላም ለማምጣት ከአዲስ አበባ ወደ ክልሉ ተጉዘዋል፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ መሪዎች ከሕዝቡ ጋር በመሥራት አብሮ መኖር በአካባቢው ረጅም ታሪክ ያለው መሆኑን በማታወስ፣ በመቻቻል የተሻለ ማኅበረሰብ መገንባት እንደሚቻል አሳምነዋቸዋል፡፡

ሙስሊሞች እና ኦርቶዶክሶች በመከልከላቸው ሙታኖቻቸውን መንግሥት በሰጣቸው መካነ መቃብሮች መቅበር አለመቻላውን ወንጌላውያን ገልጸዋል፡፡ በህዳር 1996 ዓ.ም በቡታጂራ አካባቢ አንድ የኘሮቴስታንት ቤተሰብ የሞተበትን አንድ ሕፃን በአካባቢው መካነ መቃብር ቀበረ፡፡ እንደተዘገበው ሙስሊሞች በወድቅት ሌሊት መቃብሩን ቆፍረው አስከሬኑን በማውጣት ከተማ ውስጥ ጥለውታል፡፡ ቤተሰቡ የደረሰውን ሁኔታ ለአካባቢው ፖሊስ እና ለቀጠናው አስተዳዳር ቢያሳወቅም፣ ችግሩን ለመፍታት ምንም ያህል እርምጃ አለመወሰዱ ተዘግቧል፡፡ በሐረር ኦርቶዶክሶች እና ሙስሊሞች

በሚጠቀሙባቸው መካነ መቃብሮች ወንጌላውያን ሙታኖቻቸውን መቅበር አልቻሉም፡፡ የአካባቢ እና የክልል መንግሥታት ለተለያዩ እምነቶች የመቃብር ቦታ ይመድባሉ፡፡ ሆኖም፣ የተለያዩ ችግሮች ይከሰታሉ፡፡ በጠቅላላው በእነዚህ ጊዜያት የአካባቢው የመንግሥት ሹማምንት ችግሩን ይመለከቱታል፡፡

ክፍል 4. የአሜሪካ መንግሥት ፖሊሲ

የአሜሪካ መንግሥት የሃይማኖት ነፃነትን ጉዳዮች፣ ሰብዓዊ መብቶችን ወደፊት ለማራመድ ያለው ጠቅላላ ፖሊሲ አካል በማድረግ፣ ከመንግሥት ጋር ይወያይባቸዋል፡፡

ማናቸውም የሃይማኖት ቡድን የሽብርተኞችን ግቦች በገንዘብ ለማራመድ በአገራቱ አማካይነት ገንዘብ አለማስተላለፉን እንዲያረጋግጥ የአሜሪካ ኤምባሲ መንግሥትን አበረታቷል፡፡ እንደዚሁም የኤምባሲው ሹማምንት ሁሉንም የሃይማኖት ቡድኖች እና በእምነት ላይ የተመሠረቱ መያዶችን ለመገብኘት በዚህ ዘገባ በተሸፈነው ወቅት ንቁ ጥረት አድርገዋል፡፡ የዋሃቢስት አካላት የሆኑ በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ላይ ተፅእኗቸውን ለማስፈን ያደረጉዋቸውን ሙከራዎች ኤምሳቢው በቅርብ ከመከታተሉም በተጨማሪ፣ ስለጉዳዩ ከመንግሥት ሹማምንት ጋር ተወያይቷል፡፡ በዚያው ቀን ኤምባሲው ሐያ ስምንት የሙስሊም ወጣቶች ምክር ቤት አባላትን ጋብዞ በጉብኝት ላይ ከነበሩት አሜሪካዊ ኢማም ዴርይል ዊይንራይት ጋር ሰፊ ውይይት አካሂደዋል፡፡ የመከላከያ ሚኒስቴር ለአፍሪካ ቀንድ ጥምር የጋራ ግብረ ኃይል (CJTF-HOA) ፕሮጀክቶች በሱማሌ ክልል ሙስሊም ማኅበረሰብ ዘንድ የአሜሪካን መልካም/ገንቢ ገጽታዎች ለማስፋፋት ጥረት አድርጓል፡፡ በኦሮሚያ ውስጥ በአሥራ ሦስተኛው ምዕት ዓመት የተመሠረተውን እና ለሙስሊሞች አንድ የመንፈሳዊ ጉዞ ሥፍራ የሆነው የሼክ ሁሴን የተቀደሰ ሥፍራ እየተጠገነ እንዲጠበቅበት በታህሣሥ 1998 ዓ.ም. ኤምባሲው 26,000 ዶላር ስጦታ ለግሷል፡፡ አምባሳደሯ በአገራቱ ዙሪያ ከሚገኙ የሃይማኖት መሪዎች ጋር በየጊዜው ስብሰባ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል፡

መስከረም 5 ቀን 1999 ዓ.ም. የተለቀቀ